# ትገርም ሻሸመኔ ! ትብስ ኮፈሌ!

የሕውሃቱ መሪ መለሰ ዜናዊ ታዋቂውን ዲፕሎማትና ደራሴ ደጃዝማች ዘውዴ ገብረሥላሴን ከጠባቦች ጎራ ለመመልመል መሞከሩ መሐይምነቱን የሚያሳይ ነው። በዕርግጥ መሐይም ደፋር ነው።ትግራይን በባህልና በምጣኔ ሐብት እንደ አይሁዶች አጠንክሮ፤ በፖለቲካው መስክ የበላይነቱ ለመያዝ እውን ለማድረግ ያዋቀረውን መዓከል እንዲመሩለት ነበር ደጃዝማቹን የጠየቀው። ፍቃደኛ አልሆኑለትም። እቅዱንም አልደገፉለትም። ይህንን ዜና በኢትዮጵያ ሳተላተ ቴሌቪዥን (እሳት) በማዳመጤ አስተያየቴን ለመስጠት ነው።የሕውሃቱ መሪ መለስ ዜናዊና ቡድኑ የትግራይን ሕብረተሰብ ከሌሎቹ ሕብረተሰቦች ነጥሎ በባህሉ በምጣኔ ሐብቱ እንዲልቅ አድርጎ በፖለቲካው መስክም በበላይነት ለመቆየት ማሰቡ የዋህነት ነው። ስለሕውሃቶች ጠባብነት ብዙ ቢባልም ሊማሩ አልቻሉም። እስቲ በሰፋት ስለሃገር ማሰብ ምን እንደሚመስልና ይህንን የሚገፉ ምን አይነት ግለሰቦች እንደሆኑ በምሳሌዎች አሣይቼ ወደዝርዝር ሐተታዬ እገባለሁ።

በእኛ አቆጣጠር 1966 ዓ ም ነበር። የሕዝብ ጥያቄዎች አደባባይ ወጥተዋል። የሃገሪቱ የወደፊት አቅጣጫ ለመተንበይ አስቸጋሪ ሆኗል። ልጅ ሚካኤል እምሩ በወቅቱ በጄኔቭ የኢትዮጵያ ባለሙሉሥልጣን አባስደር ነበሩ።ዶክተር ተሰፋዬ ደበሳይን ጠርተው ሰለሃገራችን ሁኔታ አንድ ነገር እንዲያደርግ ጥያቄ አቅርበውለት እንደነበር 'ያ ትውልድ' በሚለው መጽሐፉ ክፍሉ ታደሰ ገልጾታል። ፕሮፌሰር አስራት ወልደየስም ውያኔና ሻዕቢያ ሃገራችንን ከተቆጣጠሩ በኋላ በአዲስ አበባ በጠሩት ስብሰበ ላይ የአዲስ አበባን ዩኒቨርሲቲ ወክለው ተገኝተው ኢሳያስ አፈወርቂን በሰም ጠርተው 'ሃገሪቱን ከምትከፋፍሏት ለምን አንተ አታስተዳድራትም' ብለው ጥያቄ አቅረውለት እንደነበር በወቅቱ በመገናኛ ብዙሃን ተገልጿል። 'አባተህ የተከፋፈለችውን ኢትዮጵያን ይቀበሉልሃል ወይ?' እስከማለተም ደርሰዋል።

አንባቢዎቼ ልጅ ሚካኤል እምሩ ና ፕሮፌሰር አስራት ወልደየስ (Nation builders) ሃገር ገቢዎች መሆናቸው አስተውሉ። መለስና የትግራይ ሕዝብ ነፃነት ግንባር ግን ሃገር አፍራሾች መሆናቸውንም አትዘንጉ ። ዶክተር ተሰፋዬ ደበሣይ ከትግራይ፤ ኢሳያስ አፈወርቂ ከኤርትራ ናቸው። ያ ለልጅ ሚካኤል እምሩና ለፕሮፌሰር አስራት ወልደየስ ከጉዳይ አይገባም። ደጃዝማች ዘውዴ ትውልዳቸው ከትግራይ ስለሆነ ይተባበሩናል ነበር የመለስ ግምት፤ የግብዝ አስተሳሰብ። በቅርቡ ደግሞ ዶክተር በረከት ሐብተሥላሴ በፃፉት መጽሐፍ ምረቃ ላይ ኢትዮጵያንና ኤርትራን አስመልክቶ ያደረጉት ንግግር የሚያስገረም ነው። ዶክተር በረከት ሐብተሥላሴ በአፄ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ ንግሥ ከፍተኛ ሥልጣን የነበራቸው፤ ለንገሡም ታማኝ አገልጋይም ነበሩ።በኋላ ላይ ለኤርትራ መገንጠል ትልቅ ሚና መጫት ጀመሩ።ስለኤርትራም ሆነ ባጠቃላይ ስለኢትዮጵያ ታሪክ በቂ እውቀት ያለቸው ፕሮፌሰር ጌታቸው ኃይሌና ፕሮፌሰር መስፍን ወልደማሪያም አንድነታችን ለሁላችን እንደሚጠቅም ቢያስረዷቸው አልተቀበሉም። ብዙ መጣጣፎች ወይይቶች አድርገው ነበር፤ አልሆነም።ከዘመናት ጦርነትና ዕልቂት በኋላ ይሄው ዛሬ ኢትዮጵያና ኤርትራ አንድ እንደሚሆኑ ተንቢየዋል። ያንን ሳያሳየኝ አይግደለኝ እስከማለትም ደርሰዋል።ይበል የሚያሰኝ ነው።
የትግራይ ቤሔርተኞች ከዚህ ምን ይማራሉ?

ያለመማራቸው መገለጫውማ ዲፕሎማቱን ደጃዝማች ዘውዴ ገብረሥላሴን በዶክተር ክንፍ አብረሃ ሥፍራ እንዲሰሩላቸው መጠየቃቸው ነው። የትግራይ ሕዝብ የባህል፣ የኢኮኖሚና የፖለቲካ መዓከል እንዲመሩ ማለት ነው። መለስ ዜናዊና ቡድኑ ለዓመታት ከመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ የሸሸጉትን ምስጢር አወጡት። አበረዋቸው እየገደሉና እያሰሩ ለኢትዮጵያን ሕዝብ ነው የምናገለግለው ይሉን የነበሩትን ሁሉ ማዕቅ አለበሷቸው። ለትግራይ አይሁድነት እንደሚሰሩ ነገሯቸው። መለስ ዜናዊና ቡዱኑ የተወለዱበትን አካባቢ ማልማታቸው ስሕተት የለውም፤ ግን በመላው የአገሪቱ ሕዝብ ሰም የአንድ የጎሣ አባል መርጦ ለማሳደግ መሥራት ለዘለቄታው መዘዝ አለው። ምዕላተ ሕዝቡ በሚረዳው ጎሣ ላይ ጥላቻን ያሳድራል።

የትግራይ ሕዝብ ከሌሎቹ ወገኖቹ ነጥሎ (ghetto) ውስጥ እንደማጎር ይሆናል። አይሁዶችም ይህ መሰል መገለል ደርሶባቸው እንደነበር ታሪክ ያወሳናል። መለስም ለትግራይ ሕዝብ የተመኘው ይህንኑ ነው። የትግራይ ሙሑራን በዘር ፖለቲካ ተጠንፍገው በዝምታቸው ጸንተው ከቀጠሉና ከማይመለስበት ደረጃ ከደረሰ በታሪክ ያስጠይቃቸዋል። ምክንያቱም ይህን የዘር ፖለቲካ ኮትኩተውና ውኃ አጠጥተው እዚህ ያደረሱት እነርሱ ናቸውና።

ስለኤርትራም ለነ ዶክተር በረከት ሐብተሥላሴ ከአርባ ዓመት በፊት ተነግሯቸው ነበር። አልመሰላቸውም። አድፍጠው በስውር ሲረዱ ቆይተው ይሄው ዛሬ ሐቁን አዩት። ወያኔም ከሰማኒያ ያላነሱ ቤሔረሰቦችን ካካተተች ሃገር ውስጥ የትግራይን ሕዝብ ነጥሎ እንደ አይሁዶች በባህል፣በምጣኔ ሐብትና በፖለቲካው ከሌሎቹ ልቃ እንድትገኝ አደርጋለሁ ማለት ቅዥት ባይሆን እብደት ነው።

ኤርትራ ለምን አንመለከትም? የኤርትራ ነፃነት ግንባር (ELF) ንቅናቄውን ሲጀምር ምጣኔ ሐብተን ነበር መፈክሩ ያደረገው፤ 'የኤርትራ ሕዝብ ከአሰብ ወደብ በቀረጥ ከኢትዮጵያ በሚያገኝ ገቢው፣ ሳይሰራ $30 ሰላሳ ብር እየተከፈለው መኖር ይችላል' የሚል ነበር። በዚያን ዘመን $30 ብር የአንድ ወታደር ደመወዝ ነበር። ይህን እውን ለማድረግ ኤርትራ ከኢትዮጵያ መገንጠል ነበረባት። ያም እውን ሆነ።ቅኝ ገዥነት፣ የፌደራሉ መፍረስ፣ የቋንቋ መጨፍለቅ፣ የባህል መጥፋት የግለሰብ ነፃነት ዲሞክራሲ ፣ፍትሕ በተግባር ቀርቶ በጹሑም የሉም። የመገናኛ ብዙሃን ጅግንነታቸውንና ድላቸውን ከማውራት ሌላ ማስተመሪያ አልነበሩም። ዛሬ የኤርትራ ወጣቶች ነፃነት ፍለጋ ሃገር ጥለው ሲኮበልሉ፣ ከሱዳን በረሃ ኮላሊታቸው እንደጥጥ፡ ጥፍጥሬ፣ እየተፈለቀቀ ተወስዶ ሬሣቸው ለአሞራ ሲጣል፤ ኩላሊታቸውን ይዘው ከሊቢያ በረሃ የደረሱ በውኃ ጥም ሲያልቁ፤ ከውኃ ጥሙ ያመለጡ በሊቢያ እስር ቤት ሲማቅቁ ፤ ከእስር ቤት ያመለጡ፤ወደ ግብጽ ተሻግረው በግብፅ መንግሥት ተይዘው ለኢሳያስ ነፍስ ገዳዮች ሲሰጡ፤ የምናየው ነው። ከግብፅ ቢያመልጡም ወደኢዝራኤል ለመሻገር ሲሉ ወይ በወሰን ጠባቂዎች ጥይት አለበሊዚያም በሲና በረሃ የአሞራ እራት ይሆናሉ።

ኤርትራዊያኑ የሚያቋርጧቸው ሃገሮች በሙሉ አረቦች ናቸው። ኤርትራ ከእናት ሃገሯ እንድትገነጠል ከክላሽ ኮፐ ጠመንጃ ቦንብ፣ ታንክ፣ የአየር መከላከያ መሣሪያዎችን ሲያቀብሏቸው ኖረው ዛሬ ነፃነታቸውን ካገኙ በኋላ ቁራሽ ዳቦና ውኃ ነሷቸው። ኢትዮጵያም ሆነች ኤርትራ ከሽንኩር መከተፊያ ቢላዋ በላይ የሡሩት መሣሪያ የላቸውም። እልህ በመግባትና ባለመደማመጥ ውጊን ሃገራችንን ሲያል አደረግናት። የአንድ ሃገር ልጆች እንደአውሬ ተባላን። ተገዳደልን። በሃገር ውስጥ የቀሩት የኤርትራ ወጣቶች ደግሞ በሳዋ በረሃ በወታደር ማሰልጠኛ ውስጥ ፍዳቸውን እያዩ ናቸው። የኢትዮጵያ ወጣቶች ዕድል ከዚህ የተለየ አይደለም። ከኤርትራውያ ጓደኞቻችን ጋራ በየሰቆቃው ሥፍራ ሁሉ አብረን ነን። በየደቂቃው በባሕር ሰምጠው የሚልቁትን በወያኔ ደህንነት የሚገደሉትን ኢትዮጵያውያን ቤት ይቁጠረው። በቅርቡ ነዳጅ በሰውነቱ ላይ አርከፍክፎ ለሕዝቦች ነፃነት ፍትሕ እራሱን ያቃጠለው መምህር የኔሰው ገብሬ በድርጊቱ ሁሉን ገልፆታል። 'አስር መጽሐፍት ከማንበብ ኢሳያስ አፈውርቂን ለአንድ ሰዓት ማዳመጥ' ያለው መለሰ ዜናዊ፤ ድንቄም መጽሐፍ ሆነች! 'ትግራይ እንደ አይሁዶች' አደርጋታለሁ ብሎልን እርፍ አለው። ልብ ያላችሁ ልብ በሉ ጆሮ ያላችሁ አዳምጡ፤ በቤሔረሰብ ሰም ከየክልሉ በተጨበረበረ ምርጫ መጥታችሁ በፓላማ የምታቀላፉ፤ በኢትዮጵያ ስም አባሰደር ነን የምትሉ፤ በሃገር ቤት የካብኔ አባላት፤ የጦር አዛዦች ፣ ብኤድን፣ አቢዲዮ የደቡብ ሕዝቦች ተብዬዎች በሙሉ አገልግሎታችሁ ለትግራይ አይሁድነት መሆነን ተረዱት። መለስ ዜናዊ ትግራይን እንደአይሁዶች በኢኮኖሚው በባህል በፖለቲካው ለማሳደግ እንደሚሠራ ነግሯችኋል።
አቶ ኢሳያስ 'እንደሲንጋቦር' አቶ መለስ አንደ አይሁድ ሲሉ።

ተገርሜ እኔም አልኩኝ 'ትገርም ሻሸመኔ ትብስ ኮፈሌ' ።ሕልም፡ ነውስ፡ ቅዥት፣የለየለት ዕብደት፤ የጨለምቶች ጨልምት፣የአይምሮ ግድፈት፤ኢትዮጵያን አውድሞ ትግራይ መገንባት። ወያኔ ኢትዮጵያን አውድሞ ትግራይ ለማልማት ያለውን ቆራጥነት ከጥንቱ ከጠዋቱ የተረዱት በጣም እጅግ በጣም ጥቂቶች ናቸው።

ለምሳሌ ፤ በዓለም አሉ ከሚባሉት አምስት (microbiologist) ሳይንትስቶች፤ ውስጥ አንዱ የሆኑት፤ ሳይንቲስት ታዬ ጥላሁን በደብረዘይት የከብቶችን ጤንነት የሚያስጠብቅ የጥናት መዓከል ለማቋቋም ወያኔ ሥልጣን እንደያዘ ጥያቄ አቅርበው ነበር። ጥያቄያቸው በወያኔ መንግሥት ዋጋ ማጣቱ ከሰሞኑ ከአቶ መለስ ዜናዊ አፍ ያመለጠው ምስጢር ምክንያቱን ፍንትው አድርጎ አሣይቶናል። ሆን ብለው ይህቺ ሃገር እንዳታሰራራ በሕቡዕ የሚጫወቱት ደባ አየነው። እኒህ ሳይንቲስት ዛሬ በወያኔ ቦንብ የሚያዘንብበትን፤ እንደሰው መኖሩ የተነፈገውን የኦጋዴንን ሕዝብ በወጣት ዘመናቸው አገልግለውታል። የኦጋዴን ሕዝብም እውቅና ሰጥቷቸው በዘር ሳይፈርጃቸው 'ልጃችንን ድረንልህ አብረሃን ኑር' እስከማለት ደርሰዋል፤ ' Ethiopian Review' በሰማኒያዎቹ በአማርኛና በኢግሊዘኛ ይታተም በነበር መጽሔት ላይ መላው የሕይወት ታሪካቸው ተገልጿል። ሌላው ደግሞ በአንድ ሌሊት በወያኔ በአንድ ቤሔር እዝ ከአራት መቶ ሰው በላይ የተጨፈጨፈበትን ምድር ጋምቤላን የተፈጥሮ ሐብቷን ሕዝቧን ተጠቃሚ ለማድረግ ኑሮ ለመታደግ ያካባቢዋ ልጅ የሆነው ኦባንግ ሜቶ ያደረገውን ጥረት የወያኔ መንግሥት ጀሮ ነስቶት ለበአዳን መሬቱ ከመሸጡ አልፎ ከትግራይ ሕዝቦች አስፍሮ ደኑን እየመነጠሩ ከሰል እያከሰሉ እንዲኖሩ ማድረግ ኢትዮጵያን ማጥፋት ወይስ ማልማት? በዚህ ማር የተቀባ መርዝ የአይሁድነት እምነት ለትግራይ ሕዝብ አይበጅም። የትግራይ ሕዝብ በባህሉ ከሌላው የኢትዮጵያ ሕዝብ የተለየ አይደለም። የወያኔ ከአርባ ዓመት ወዲህ የሚያራምደው ባህል የትግራይ ሕዝብ ባህል አይደለም።

ዋናዎቹ መሪዎቹ ያ ደረጉትንና እያደረጉ ያሉትን መጥቀስ ይቻላል። በትግራይ ሕዝብ ስም የሚቀሳቀሱት ሹማምት በሙሉ ይዋሻሉ፤ ዋሽተውም ያስዋሻሉ፤ ለቤተክርሲቲያ ሆነ ለመስኪድ ክብር የላቸውም ፤ የቤተክርስቲያነ መስቀል፣ አላባሳትን፣ ታቦታት ሳይቀሩ አውጥተው ይሸጣሉ።ግብረ ሶዶምነት ባህላቸው ነው። በመሐል ሃገርም እያስፋፉት ነው።ለሴት ልጆች ክብር የላቸውም፤ እነርሱ አዲስ አበባን ከተቆጣጠሩ ወዲህ ሴት ልጆች በአሲድ በጩቤ በጥይት ሲገደሉ አየን፤ እርስ በእርስ መገዳደልን ከደደቢት ይዘውት የመጡት ባህል መሆኑን ሕዝብ የሚያውቀው ነው።በዱር ያደረጉትን በከተማ ደገሙት። ለምሳሌ ስዩም መስፍን በሽሽግ ሩካቤ ሥጋውን አርክቶ የተወለዱትን ሕፃናት ቀምቶ ሴቶቹን በጦር ሜዳ አዲሞቱ ማድረጉን አቶ ዘላለም መኮንን በእሳት ላይ ባደረጉት ወይይት ግልጸውታል፤ በዶክተር ክንፉ አብረሃ ቦታ ተክቶ የሚሠራው ሰባት ነጋም ኪዳን የሌለው ከጋብቻ ውጭ የወለዳቸውን ልጆች ከዶ ለእናቶቻቸው ማሳደጊያ ከልክሎ በመንገድ ላይ ተቀምጠው እንዲለምኑ ያደረገ ሰብአዊነት የማይሰማው ግለሰብ ነው። ይህ ሰው የትግራይ የባህል፣ የምጣኔ ሐብትና የፓለቲካ መዓከል ተጠሪ ሆኖ መቀመጥ ለማስተማር ወይስ ለማደናገር? ሥልጣኑን መከታ አድርጎ ከልጅ ልጆቹ እኩያዎች ጋር አንሶላ የሚጋፈፍ፤ ባህል የለሽ የባህል መሪ ነው። ለትግራይ ሕዝብ መሰደቢያና ማፈሪያ ነው። ከጣሳ ጠላ ወደ ጀሪካን ውስኪ የተሸጋገረ የመጠጥ ሱሰኛ እንዴትስ ለትግራይ ወጣቶች ምሳሌ ሊሆን ይችላል? በፊርማው ያስጨረሳቸው የትግራይ ወጣቶች ደም ከባዶ ስድስት ይጣራል።

በምጣኔ ሐብቱ ዘርፍ ኤርትራ በወቅቱ በአሰብ ወደብ ተመክታ ነበር። ትግራይስ በምኗ ትመካለች? በኢፈርት አይን ባወጣው ሌባ ድርጅት ወይስ የኢትዮጵያን ወጣት ሴቶችን ለአረቦች በመሸጥ ከሆነ ያም ውርደት ነው። ውርቅን በባሌስትራ ቀይሮ ከባንክ በማኖር ፤ ቡና ከመጋዘን አዘርፎ በመሸጥ የምጣኔ ሐብት የበላይነት ሊመጣ አይችልም።

መለስ ዜናዊና ቡድኑ በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ የፖለቲካውን የበላይነት ከያዙ ይሄው ሃያ ዓመት ሞላው። ኢትዮጵያን ለማዳከም ትግራይን ለማጎልበት ከሆነ ብዙ ዓመት ይቀራቸዋል። ኤርትራ ለማስገንጠል ተዋጉ፤ በተባበሩት መንግሥታት ከማንኛውም አባል በፊት ለኤርትራ ዕውቅና ሰጡ። 'አማራና ኢትዮጵያዊ የሚባሉትን አከርካሪያቸውን ሰበሩ።የኢትዮጵያን ሠራዊት በትግራይ ቤሔረሰብ ሰራዊት ተኩት። ሌላው ሕብረተሰብ እንዳያንሰራራ በቤሔረሰብ ተከፋፍሎ፤ ኬላ ተበጅቶለት፤ እርስ በእርሱ እንዲቆራቆስ እየተደረገ ነው። በሃይማኖት፣ በ ዘር፣ በፓለቲካ፣ ክፍፍሉ ተጧጡፏል። ሥረዕተ ትምህሩት ትኩረት የለሽ እንዲሆን ተደርጓል፤ ዩኒቨርሲቲ ገነባን ሲባል የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ግንባታው ቆሟል። የሞያ ማህበራት ፈርሰዋል። የሥራ ቦታዎች የካድሬ ማምረቻ ሆነዋል፤ የሃገርን መሬት ከዜጋው ተቀምቶ ለባዕዳን ተሸጧል፤ የሃገር ወሰን ተደፍሯል። ተልዕኮዎ ትግራይ ለማሳደግ ኢትዮጵያን ለማጥፋት ከሆነ በመጠኑም ቢሆን ተሳክቷል።

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በማርቆስ ወንጌል ምዕራፍ 19 ቁጥር 14ላይ፤
ጽዋውን አንስቶ ለደቀመዛምርቱ አላቸውም፣ ይህ ደሜ ነው ላዲስ ሥረዕት ስለብዙ የሚፈስ።
የኢትዮጵያን ራዕይ የመምህሩ የኔሰው ገብሬ ራዕይ ይሆን? ላዲስ ሥረዕት ስለብዙ የሚፈስ።
ኢትዮጵያን እግዚአብሔር ይጠብቅ።

በየአላችሁበት መልካም ገና ይሁንላችሁ።

ታደለ መኩሪያ
tadele@shaw.ca